# መልከዐ ቅዱስ ሚናስ

1. የይሁዳና የሌዊ መመኪያ ማርያም ሆይ፣ በሰነፎች እንደበት ጥበብን የምታዘጋጂ/የምታኖሪ/፣ የሃይማኖት መንፈሳዊ መልሕቅ የሆነ ለወዳጅሽ፣ የሚናስን ያለ/የታወቀ/ ገድሉንና ትሩፋቱን፣ እናገር ዘንድ በእኔ በአገልጋይሽ ላይ፣ የሃይማኖትን ጠል ከሰማይ አውርጅልኝ/አፍስሺልኝ።

2. ለዝከረ ስምከ ፣ ሚናስ ሆይ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ለተዋሐደ፣ ክርስቶስ ለተባለ ለእግዚአብሔር በሕጉ ሰሌዳ ለይ ለተቀረጸ ፤ ስም አጠራርህ ስለምታ ይገባል፤ የውስጥና የውጭ ሥር የሰማዕት አለቃ ሚናስ ሆይ ፤ የተሰወረ ገድልህን በአንደበቴ አገልጽ ዘንድ ፤ በልቡናዬ ውስጥ የቀና እውቀትን/መንፈስን/ አድስ።

3. ለስእርተ ርእስከ፣ ሚናስ ሆይ ለራስህ ሁለተኛ ለሚሆን ፤ ለራስ ጸጉርህ ሰላምታ ይገባል፤ መልኩ ከመስታዎት ለሚያበራ፤ ፊትህንም ሰላምታ ይገባል የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዙን የፈጸምክ፤ ሚናስ ሆይ ክፉ ልማድና ባህል ያላቸው በእኔ ላይ ቢነሱ፤ ጌታዬ ሚናስ ሆይ አንተ ወደ ኋላ እንዲመለሱ አድርጋቸው።

4. ለቀራንብቲከ፡ ሚናስ ሆይ እንደ አጥቢያ ኮከብ ለሚሆኑ አይኖችህና፤ ለአይኖችህ ቅንድቦች ሰላምታ ይገባል የንጉሥ ክርስቶስ ፤ ትዕዛዝ ለሚሰሙ ጆሮችህም ሰላምታ ይገባል፤ በሰማዕትነት በምስክርነት ደም የተረጨህ ሚናስ ሆይ፤ ኃጢአተኛ አገልጋይህን ርኩስ ከሆነ ከኃጢአት ጥፋት አንጻኝ/እጠበኝ/።

5. ለመላትሒከ፡ ሚናስ ሆይ ቅላቱ ከሮማን ቅላት ለሚቀሉ ጉንጮችህ፣ ሰላምታ ይገባል፤ የገነትን መዓዛ ላሸተቱ አፍንጮችህም፣ ሰላምታ ይገባል፤ የተመረጥክ የእግዚአብሔር ምስክር ሚናስ ሆይ ፤ ከዚህ አለም ገዥ ከዲያብሎስ አድነኝ ተቤዠኝ ሥራን ክፉና ጎዳናው፤ ጠማማ ከሆነ ከዲያብሎስ ፈፅመህ አድነኝ።

6. ለከናፍሪከ፡ ሚናስ ሆይ በየእለቱ ስድብን ላልተናገሩ ከንፈሮችህ ፣ ሰላምታ ይገባል፤ የቃል ኪዳን ወዳጅና የነፍሴ ወዳጅ አንተ ፣ ጌትነትን ክብርን የተመላ ጌታህ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ፣ እኔ አገልጋይህን ታድነኝ ዘንድ በጸሎትህ ተማፅኛለሁ።

7. ለአፉከ፡ ሚናስ ሆይ ከስባቱ ልቃነ መላዕክት ጋር ከሥላሴ ፊት ፤ ቆሞ ምስጋናን ላላቋረጠ አንደበትህ/አፍህ/ ሰላምታ ይገባል ፤ የካህናት አለቃ ሚናስ ሆይ ፣ በሙሴ ወንድም በአሮን አምሳል ፤ በደለኛ ብሆንም ሕጢአቴን አስተስርይልኝ ፤ በላም ደምና ስብ ሳይሆን በክህነትህ።

8. ለአስናኒከ ፡ ሚናስ ሆይ ከአንደበትህ ጋር ለጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል ፤ በአደባባይ መካከል የከሐድያንን ነገር ለሚቃወም ቃልህም ሰላምታ ይገባል ፤ ለሚመጣ ዓለም ለመንግስተ ሰማያት አገልጋይ አድርገኸኛልና ፤ ከሰማዕታት ጋር ታምራትን እያደረግህ ፤ ዘወትር ሕዋሳቶቼን /ሰውነቶቼን/ ገስጽ።

9. ለእስትንፋስከ ፡ ሚናስ ሆይ እንደ አፈውና ርኄ እንድተባሉ ሽቱዎች ፤ በአራቱ ማዕዘን ለሚአውድ እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል ፤ ኤሎሄ የተባለ የኢየሱስ ምስክሩ የተመርጥከ ሚናስ ሆይ ፤ በቤተ መቅደስህ ምስጋና የሚያቀርቡትን ባርካቸው ከጥፋትም አድናቸው።

10. ለጉርዔከ፡ ሚናስ ሆይ ከሮም ሰዎች ወይን ጣዖት ፤ ለራቀ/ለተከለከለ/ ጉሮሮህ ሰላምታ ይገባል ፤ የሰላም ሰው እንደሆነ እንደ መርቆሬዎስ መከራን የታገስከ ሚናስ ሆይ ፤ ሰነፍ/ቸልተኛ/ እንደ ምሆኔ ከንዋመ ኀኬት አንቃኝ።

11. ለከሳድከ፡ ሚናስ ሆይ በወገብህ መሐል ለተተከለና ለለመለመ አንገትህ ሰላምታ ይገባል ፤ ሚናስ ሆይ ከሰማዕታት ጋር ጉባኤ አድርገህ/አንድ ሆነህ/ ፤ እኔን ሊያጠፉ የሚወዱ ጠላቶቻችን ብትናቸው ፤ በአንገታቸውም የተሳለ ሰይፍህን አውርድባቸው።

12. ለመታክፍቲከ፡ ሚናስ ሆይ ክርስቶስ በሊቶስጥራ የተቀበላቸውን መከራዎች ፤ በአደባባይ ለተቀበሉ /ለተሸከሙ/ትከሾችህ ሰላምታ ትገባል ፤ ከብዙ ጭፍሮች/ወታደሮች/ የተመረጥከ ሚናስ ሆይ፤ ከመከራ ሁሉ አድነኝ ተቤዠኝ ፤ ከተሰወረ ከሰይጣን ከሲሳራ ስይጣን መከራ አድነኝ።

13. ለዘባንከ፡ ሚናስ ሆይ በደብረ ሲና የፈጣሪ ፀጋ እንደ ተመላ ፤ እንደ ሙሴ ለተመሰገነ ደረትህና ጀርባህ ሰላምታ ይገባል ፤ ሚናስ ሆይ ጌታህ ክርስቶስ የመንግስተ ሰማይን ሰርግ ባደረገ ጊዜ ፤ ሰባት ጊዜ ሰባ ብበድልም ከአንተ ጋር አስቀምጠኝ እኝጂ በውጭ አትተውኝ።

14. ለሕጽንከ፡ ሚናስ ሆይ ለሕጽንህና/ለብብትህ/ ለሁለት እጆችህ፣ ሰላምታ ይገባል ፤ ለእጆችህና ክፍሉ ለሆነ ክርንህ/ክንድህም/ ሰላምታ ይገባል ፤ የእስጢፋኖስና የቂርቆስ ውዳጃቸው የምትሆን ጌትዬ ሚናስ ሆይ፤ ይህ ፍቅረኛዬና ወዳጄ ነው እያልክ በከንቱ እንዳልጠፋ አደራ አስጠብቀኝ።

15. ለእሙትከ፡ ሚናስ ሆይ ያለና ተስፋ ስለሆነ ሃይማኖይ ፤ ለታሰሩ እጆችህና መዳፎችህ ሰላምታ ይገባል ፤ የትጉሀን መላዕክት ወዳጅ ሚናስ ሆይ ፤ ኃጢአተኛ አገልጋይህን የተናቅሁ እኔን ፤ ከዘመኑ ሐሰተኛ ሰው ሰውረኝ አድነኝ።

16. ለአጽብዒከ፡ ሚናስ ሆይ በሕይወት አምሳል ፤ ዘወትር ከሚለመልሙ ጥፍሮችህ ጋር ለጣቶችህ ሰላምታ ይገባል ፤ እንደ ፋሲለደስ ምስክር የሆንክ የተመረጥክ ሚናስ ሆይ ፤ ጌታህ ክርስቶስ ምዕመናንን ከሰይጣን ወጥመድ እንደ አዳናቸው ፤ እኔ አገልጋይህን ከጥፋት ሁሉ አድነኝ ተቤዠኝ።

17. ለተቀስፎትከ፡ ሚናስ ሆይ ከሆድህ ጋር አንድ ለሆነ/ለተዛመደ/ ጎንህና፤ ለግርፋቶችህ ቁስል ሰላምታ ይገባል የጊወርጊስ ወገን ሰማዕት ሚናስ ሆይ ፤ አስቀድሞ የሕዝቡ የምዕመናን መምሕር ሦስት ቀን እንደተሰውረ ፥ ከፀብና ከጥፋት በረድኤትህ ሰውረኝ።

18. ለኩልያቲከ፡ ሚናስ ሆይ ሟች ለሆነ ሰው/በሞት ለሚለወጥ ሰው/ ፤ መንግስተ ሰማያትን ለሚያድል ሕሊናጎና ሁለቱ ኩላሊቶችህ ሰላምታ ይገባል ፤ በጳውሎስ አምሳል /እንደጳውሎስ/ የምታመሰግን የሽቱ መዓዛ ሚናስ ሆይ ፤ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ታከብርሀለች ፣ ታመስግንሀለች፤ በሰማዕትነት ደምህ የተወደደ ልጇ ሆነሀታልና።

19. ለአማዑቲከ፡ ሚናስ ሆይ የሕጓ ሥርዓት የተወደደ ከሆነላት ፤ ከሙሴ ድንኳን አንድ ለሆነና ለተከማቸ ፤ ለውስጥ ሕዋሳትና አማዑትህ ሰላምታ ይገባል ፤ በትዕግስትህ ከኢዮብ ትዕግስት ጋር አንድ ለምትሆን ሚናስ ሆይ ፤ ያለ መጉደልና ያለ ሐፀፅ መከራን እቀበል ዘንድ አብቃኝ ፤ ከአለም ከፋትም ነፃ የወጣሁ አድርገኝ።

20. ለጎንብርትከ፡ ሚናስ ሆይ ሥላሴን ሲያመሰግን ምስክርነትንና ገድልን እንደ ዝናር ለታጠቀ ፤ ወገብጎና እንብርትን ሰላምታ ይገባል ፤ ትዕግስትን እንደ ልብስ የለበስክ ፤ ጳውሎስ የተባልክ ሚናስ ሆይ ፤ መከራ ቢመጣብኝ ድንገትም ቢከበኝ ፤ ትዕግስትን /አርምሞን/ ስጠኝ ዳግመኛም ፀጥታን ጽናትን ስጠኝ።

21. ለዓቍያጺከ፡ ሚናስ ሆይ በጠራ ሰማይዊ ቀለም ለተሰራች ፤ ለአርጤምስ ጣዖት ላልሰገዱ ጉልበቶችህና ወገቦችህ ሰላምታ ይገባል ፤ የመርዩጥ መመኪያ አፀደ ሰማዕት ሚናስ ሆይ ፤ ፍርድን በቀል በተደረገበት ዕለት አድነኝ ፤ እናት የወለደቻት ልጇን ማዳን ባማትችልበት ቀን ተቤዠኝ።

22. ለአዕጋሪከ ፡ ሚናስ ሆይ በገድልና በምስክር አጸዶች ውስጥ ዘወትር ለተመላለሱ እግሮችህ ከተረከዞችህ ጋር በአንድነት ሰላም ይገባል ፤ ምሁር ያደርግሁህ የኪዳኔ ወዳጅ ሚናስ ሆይ ከአንተ ሌላ ምሁርን አጥቻለሁና ጸሎቱን የተወደደ ልመናየንም የሰመር አድርገው ፤

23. ለመከየደከ፡ ሚናስ ሆይ ለእግሮችህ ጫማዎችና ለጣቶችህ ከጥፍሮችህ ጋር ሰላምታ ይገባል ፤ ዳግመኛም ለቁመት አካልህና ከቡር ለሂነ መልክህ ሰላምታ ይገባል ፤ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሰማዕት ሚናስ ሆይ ትንሳኤ ሙታን የለም ብለው ከሚክዱ ጠላቶች በጸሎትህ ጋሻ ሰውረኝ ከዚህ ዓለም ደግ ሰው አልቋልና።

24. ለፀዓተ ነፍስከ፡ ሚናስ ሆይ በመንግስተ ሰማይ ከተሰበሰቡ ሰማዕታት ጋር የማያልቅ ተድላ ነፍስን ታደርግ ዘንድ ከስጋህ ለተለየች ነፍስህ ሰላምታ ይገባል ፤ ሚናስ ሆይ በሰማዕትነት ቀን በአቅራቢያህ የነበሩ በአርያም/በሰማይ/ ያለውን ምስጢር ሲያዩ እንዲህ ተባባሉ ልብሱንና ሰውነቱን በበጉ ደም ያጠበ ከሚስርቁም ፈፅሞ የጠበቀ ይህ ነው አሉ።

25. ለብድነ ሥጋከ፡ ሚናስ ሆይ ለስጋህ በድንና በበፍታህ ለሚሆን ግንዘትህም ሰላምታ ይገባል ፤ ዳግመኛም ኀትምት መቃብርህም ሰላምታ ይገባል ፤ የሰማዕታት አለቃ የተመረጥህ ሚናስ ሆይ በዚህች ዕለት ዝክርህን ያደርጉትን ከመከራ ጥፋት ሁሉ አድናቸው ተቤዣቸው።

26. ናሁ ተፈጸመ ፡ ሚናስ ሆይ ድዳና እንደበቱ ኮልታፋ የሆነ አገልጋይህ የውዳሴህን/ምስጋና/ መልክ በየወገኑ በየሥርዓቱ እነሆ ፈፀመ/ፈፀምኩ/ ፤ ሚናስ ሆይ በአብርሃም እቅፍ የተቀመጠች ነፍሴ በእሳቱ ነበልባል እንዳትቃጠል የይቅርታህን ጠል ከሰማይ በእኔ ላይ ላክ። ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።